የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የምርምር አመራር ምደባ መመሪያ

ቁጥር …. /2016

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የአገራችንን የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ለማሳደግ የሚያስችሉ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ለግብርና ልማት ተጠቃሚዎች በማድረስ ረገድ ከፍተኛ ሀገራዊ ተልዕኮ የተሰጠው ~~ተቋም ሲሆን~~ ኢንስቲትዩት ሲሆን ይህንኑ ተልዕኮ ለመወጣት ተቋማዊ አደረጃጀቱን በየጊዜው እየፈተሸ ማሻሻል እንዲሁም አደረጃጀቱን በብቃት የሚያስፈጽም የምርምር አመራር መመደብ አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡

~~በዚሁ መሰረት~~ በመሆኑም ከዚህ በፊት በኢንስቲትዩቱ ፀድቆ በሥራ ላይ የዋለው የምርምር አመራር ምደባ መመሪያ በትግበራ ሂደት በርካታ ክፍተቶች ያሉት መሆኑን በመፈተሽ እነዚህን ክፍተቶች በሚያርም መልኩ መመሪያውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም በሥራ ላይ ባለው መመሪያ ላይ ያጋጠሙ ክፍተቶችን ማለትም አንዳንድ የመመዘኛ መስፈርቶች ግልጽ ያለመሆን እና ለአሰራር አመች ሆነው አለመገኘታቸው፤ በመመሪያው ውስጥ የምርምር አመራርን የማይመለከቱ የምደባ መስፈርቶችን ማስተካካል በማስፈለጉ፤ መመሪያው የምርምር ዳይሬክተሮችን አመዳደብ ብቻ የያዘ በመሆኑ ሌሎች የምርምር አመራሮችን ለመመደብ የሚያስችል አለመሆኑ እንዲሁም ከጊዜው ጋር የሚሄዱ አዳዲስ አሰራሮችን በመመሪያው ውስጥ ማካተት በማስፈለጉ በኢንስቲትዩቱ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 527/2015 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 21 በተሰጠው ተቋማዊ የአሰራር ስርዓቶችን የመዘርጋት ሥልጣንና ተግባር መሰረት ይህ የምርምር አመራር ምደባ መመሪያ ተሻሽሎ ወጥቷል፡፡

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የምርምር አመራር ምደባ መመሪያ ቁጥር …. /2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አንቀጽ 2

ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

2.1 የምርምር አመራር፡- ማለት አንድን ዳይሬክቶሬት ወይም ማዕከል ወይም ፕሮግራም እንዲመራ ኃላፊነት ወይም ውክልና የተሰጠው ግለሰብ ማለት ነው፡፡

2.2 የበላይ አመራር፡- ማለት በመንግሥት የተሾሙትን ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ማለት ነው፡፡

2.3 ዳይሬክቶሬት፡- ማለት በኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት የሚገኝ አንድ ራሱን የቻለ ተግባር እንዲያከናውን ወይም በማዕከላት ተመሳሳይነት ያላቸውን ተግባራት የሚያከናውኑ ቡድኖችን የሚመራና የሚያስተባብር፣ ለሥራ ማስኬጃ የሚሆን በጀት የተመደበለት በሕግ አማካይነት ወይም በኢንስቲትዩቱ ውሳኔ የተከፈተ ክፍል ማለት ነው፡፡

2.4 ኃላፊ፡- ማለት እንደአስፈላጊነቱ በየደረጃው ከቡድን መሪ እስከ ተቋሙ የበላይ አመራር ያሉትን ያጠቃልላል፡፡

2.5 የቡድን መሪ፡ -ማለት በኢንስቶትዩቱ ስር ካሉ የምርምር ዘርፍ ወይም ከሥራ አስፈጻሚዎች ስር የተደራጀ የስራ ፈጻሚ ሠራተኞችን በቅርበት የሚከታተል ባለሞያ ማለት ነው፡፡

2.6 ፕሮግራም፡- ማለት በአንድ የምርት ዓይነት ወይም ዘርፍ ላይ የሚደረግ የምርምር ሂደት ሆኖ በስሩ በርካታ የምርምር ፕሮጀክቶችን እና ሥራዎችን የሚይዝ ነው፡፡

2.7 ማዕከል፡- ማለት በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ሥር የሚተዳደር የግብርና ምርምር የሚካሄድበት ቦታ ማለት ነው፡፡

2.8 ምደባ፡- ማለት በተቋሙ የበላይ አመራር አንድን ዳይሬክቶሬት ወይም ማዕከል ወይም ፕሮግራም እንዲመራ የታመነበት ግለሰብ በቀጥታ የሚሰጥ ውክልና ማለት ነው፡፡

2.9 ውድድር፡- ለምርምር አመራር መምራት ለሚችሉ ብቃት ላላቸው ተወዳዳሪዎችን ግልጽ ማስታዋቂያ ወጥቶ ባላቸው የትምህርት ዝግጅት እና የሥራ ልምድ ተወዳዳሪው የሚመደቡበት ሂደት ነው፡፡

2.10 ምርጫ፡- ማለት አንድን የምርምር አመራር በስሩ ባሉ ሠራተኞች ምርጫ እንዲካሄድ በማድረግ የተሻለ የትምህርት ዝግጅት፣ ልምድና ክህሎት ያለውን ግለሰብ የማስመረጥ ሂደት ነው፡፡

2.11 አስመራጭ ቡድን፡- ማለት የምርምር አመራርን ምርጫ በገለልተኝነት ለማከናወን ከዋና መሥሪያ ቤት ወይም እንዳስፈላጊነቱ ከሌላ ማዕከል በኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራር የሚመረጥ ኮሚቴ ነው፡፡

2.12 የምርጫ ታዛቢ፡- ማለት በምርምር አመራር ምርጫ ወቅት ያለውን ሂደት ገለልተኛ ሆኖ እንዲታዘብና እንዲከታተል ከዳይሬክቶሬቱ ወይም ከማዕከሉ ወይም ከፕሮግራሞ ሠራተኞች መካከል የሚመረጥ ቡድን ነው፡፡

2.13 መምረጥ የሚችል ሠራተኛ፡- ማለት ኢንስቲትዩቱ ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ሠራተኛ ነው፡፡

2.14 መለስተኛ ማዕከል፡- ማለት ለአንድ ማዕከል ተጠሪ ሆኖ የተቋቋመ የግብርና ምርምር ~~ማካሄጃ ቦታ ወይም መካን~~ የሚከናወንበት ስፍራ ማለት ነው፡፡

2.15 አንድ የአገልግሎት ዘመን፡- ማለት ሦስት ዓመት ነው፡፡

2.16 ኢንስቲትዩት፡- ማለት የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ነው፡፡

2.17 ጾታ፡- በዚህ መመሪያ በማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው ሁሉ የሴት ጾታንም የሚያጠቃልል ነው፡፡

አንቀጽ 3
የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የምርምር አመራር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 4
የምርምር ዘርፍ አመራር ተግባርና ኃላፊነት

4.1 በአገሪቱ የሣይንስና ቴክኖሎጂ፣ የግብርና ልማት ፖሊሲዎች መሠረት የምርምር ዘርፉን ስትራቴጂ ይነድፋል፣ ቅደም ተከተል ይወስናል፣ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ያወጣል፣ ሲፀድቅም በሚመለከታቸው ፕሮግራሞች በኩል ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

4.2 ከአገሪቱ የልማት አቅጣጫ እና ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ የምርምር ሥራዎችን ይቀርጻል፣ ይገመግማል፣ ያፀድቃል፣ በበጀት በመደገፍ በፕሮግራሞች በኩል ተግባራዊ ያደርጋል፤

4.3 ለተጠናቀቁ የምርምር ሥራዎች የግምገማ መድረክ በማዘጋጀት ያስገመግማል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ውጤቶቹም እንዲታተሙ ያደርጋል፤

4.4 ከምርምር የሚወጡ ቴክኖሎጂዎችንና መረጃዎችን በዕቅዱ መሰረት መውጣታቸውን ያረጋግጣል፣ ለተጠቃሚዎችን እንዲደረሱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

4.5 ወቅታዊነት ባላቸውና ዘርፉን በሚመለከቱ አጀንዳዎች ላይ አገራዊ አውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት ለልማቱ ፈጣን የመረጃ አቅርቦት እንዲኖር ይሰራል፤

4.6 ከዳይሬክቶሬቱ የሚገኙትን የምርምር ውጤቶች መሰረት በማድረግ ልማቱን የሚያግዙ የአመራረትና የአሰራር መመሪያዎችን ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፣ ለቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎችና ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፤

4.7 የምርምር ስርዓቱን ለማዘመን የሚያስችሉ አዳዲስ አሰራሮችን እና ቴክኖሎጂዎች ለመጠቀም እንዲቻል የአቅም ግንባታ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፤

4.8 በዳይሬክቶሬቱ የሚመነጩትን አዳዲስ የምርምር መረጃዎች (ዳታ) ወደ መረጃ ቋት ሥርዓቱ እንዲገቡ ያደርጋል፤ በጥቅል መረጃዎቹ ላይ አዳዲስ ትንተናዎችን በመስራት የግብርና ችግሮችንና መፍትሄዎችን ሞዴል በማድረግ ይሰራል፤

4.9 ከሌሎች የምርምር እና ልማት አጋር አካላት ጋር በትብብር ይሠራል፤

4.10 ለዳይሬክቶሬቱ ተጨማሪ ኃብት ያፈላልጋል፣ ያመነጫል፤

4.11 በዳይሬክቶሬቱ ስር ያሉ የፕሮግራም አስተባባሪዎችን የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፤ ክፍተታቸውን እየለየ ድጋፍ ያደርጋል፤

4.12 ዳይሬክቶሬቱን ወክሎ በኢንስቲትዩቱ የማኔጅመንት ስብሰባ ላይ ይሳተፋል፤

4.13 የምርምር ፕሮግራም አስተባባሪዎች እንዲሚሉ ያደርጋል፣ በጊዜያዊነት አስተባባሪዎችን ይመድባል አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

4.14 የዳይሬክቶሬቱን የሰው ኃይል ያስተዳድራል፣ አስፈላጊ ሲሆን በክፍት ቦታዎች ሠራተኛ እንዲሟላ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤

4.15 ሌሎች ከሚመለከተው የበላይ ኃላፊዎች የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 5

የምርምር ማዕከል ዳይሬክተር ስልጣንና ኃላፊነት

5.1 uU`U`□ የድጋፍ ሰጪ Y^ ዘርፎ9 S"ቦM p ጅታዊ :c^` በመፍጠር የሥራ ሂደ□9 ውጤታT እ ዲሆ□ ያደርጋል፤

5.2 ማዕቦK‹ የተሰጠው የሥራ ድርሻ በመተግበር የሚጠበቅበ ውጤ ለማስመዝገብ ይ0 ለው ዘ ድ በማዕቦM የሚገ□ው የፋይ□ e' የሰው ኃይል□ ቁሳዊ Gw :k□ጅ□ በጋራ ለመጠቀም የሚያስ9 ል ውጤታማ፣ ወጪ ቆጣቢ□ ፍ ሃዊ :ሰራር ያሰፍ□M&

5.3 የማዕቦK‹ Gw□9 ቦብክ□ ፣ ቦS‹e□ እና ብልሹ :c^` በፀዳ SMቦ‹ KታKSL ው ተግባር መዋላ ው ም ይቦታተላል፣ ያረጋግጣል፤

5.4 ቦማዕቦK‹ ተገልጋዮ9□ ባለድርሻዎ9 ጋር የጠበቀ ግ□ ‹□ በመፍጠር የምርምር ሥራው በተጠቃሚ ፍላጎ ላይ እ ዲሆ ቦዕቅድ ጀምሮ eቦ □ክካሎጂ :p`x ድረስ ሂደቱ ይበልጥ :d ፊ ለማድረግ ቦ}sS‹ :ሰራር ጋር በተጣጣመ መልቡ የማዕቦK‹ S`G ግብር uSp[ጽ ይተገብራል፣ ይቦታተላል ያስፈጽማል፤

5.5 የማዕቦK‹ }S^T]-9 uTe}vu` u}sS‹ ቦሚወጡ :ዳዲስ □ክኖሎጃች ውስጥ K፡ ካባቢው‹ }eTT፥ የሆ□ የምርምር ውጤ□9 በመለየ ለተጠቃሚ-9 እ ዲተዋወቁ ያደርጋል፣ :ፈፃጸሙ ይቦ }LM፣ ይቆጣጠራል፤

5.6 ደጋፊ የሥራ ሂደ□9 የሚሰጧ ው :ገልግሎ□9 ቀልጣፋ በመንግስት ህግና ደንብ እንዲሁም u፡፡ e+ ዩቱ SW[መፈጸማ ው ያረጋግጣል፤ይቦ }LM&

5.7 የማዕቦM MT □ □ክካሎጂ ብዜ ማስተባበሪያ የተቀላጠፈ :ገልግሎ በተፈለገበ ወቅ መስጠ ዲ9 M G‹□ -9 ያመ00 M& :ፈፃፀሙ ም ይቦ }LM& ይቆጣጠራል

5.8 u፡፡ e+ ዩቱ ሀገራዊ ዕቅድ SW[በማዕቦM የሚጠበቀው ዓመ ዊ የ□ክካሎጂ ብዜ □ :p`x ዲቦ□ወ ያደርጋል፣ :ፈጻጸሙ ይቦ ተላል፣ ያረጋግጣል፤

5.9 የ፡፡ ፎ`T፧i□ ኮሙ□ቦ፧i □ክካሎጂ በተሟላ መልቡ ጥቅም ላይ ዲውል :ስፈላጊው ድጋፍ ያደርጋል፣ ይቦ }LM፣ ያረጋግጣል፤

5.10 የ፡፡ e+ ዩቱ የበላይ :S^` uTTቦ` ማዕቦK‹ ወክሎ □ ጉዳዮ9 ይሳተፋል፤

5.11 የማዕቦሉ የሥራ ሂደ□9 ' wN፧^ዊ የምርምር ፕሮግራም :e}vv]ዎ9 ቦ፡፡ e+ ዩቱ የሥራ ዘርፎ9 በተዋረድ የተሰጣ ው e ^□ጂያዊ ግቦ9 ዕ ዲያሳቦ‹ G‹□ -9 ያመ00 ል፣ ሙሉ ድጋፍም ያደርጋል፤

5.12 የማዕቦK‹ የምርም`□ የድጋፍ ሰጪ Y^ ዘርፎ9 የ፡ ፈጻጸም ሪፖር u}SKቦ} S`G ግብር መሠረ K}sS‹ T□ጅመ በወቅቱ ያቀርባል፤

5.13 የማዕቦK‹ የማ□ጅመ ቡድ በበላይ□ ይመራል፤ ተቀመጠው S` -ግብር SW[ የ ቅድ ክ ው :ፈጻጸሙ ይገመግማል፣ ወቅ ዊ የማሻሻያ□ እ`U ርምጃ ይወስዳል፤

5.14 uY^ ላይ የሚያጋጥሙ የምርምር፣ የ፡ ገልግሎ :ሰጣጥ□ የዲሲፕሊ ጉዳዮ9 ደ :ስፈላጊ□ ቦማዕቦK‹ የማ□ጅመ ቡድ ጋር uSJ S`Ua በወቅቱ የመፍ H፧ ርምጃዎ9 ይወስዳል፣ ለበላይ ላፊም ሪፖርር ያቀርባል፡፡

5.15 የለውጥ ፕሮግራሞችን ማለትም መሠረታዊ የሥራ ምዘና ለውጥ፤ ሚዛናዊ ስኮር ካርድ፤ የቡድንና የማዕከል ቻርተሮች፤ የዜጎች ቻርተር የመሳሰሉትን በተግባር መዋላቸውን በበላይነት ይከታተላል፤ የሠራተኞች የሥራ አፈጻጸም ወቅታዊ ግምገማ መደረጉን በዚህም ተአማኒነት ያለው በውጤታማነት ሠራተኞችን ሊለይ የሚችል አካሄድ ተከትሎ መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

5.16 በማዕከሉ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ያደርጋል፤

5.17 በየዘርፉ የማዕከሉ የሥራ ዕቅዶች ተተንትነው ለእያንዳንዱ ሠራተኛ መውረዳቸውን በበላይነት ይከታተላል፣ ይመራል፤

5.18 በማዕከሉ ኪራይ ሰብሳቢነት እንዳይኖር፤ ድርጊቱን ሠራተኛው እንዲታገለው ጥረቱን በበላይነት ያስተባብራል፤

5.19 ሌሎች ከከኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 6

የፕሮግራም አስተባባሪዎች ተግባርና ኃላፊነት

የፕሮግራም አስተባባሪዎች ተጠሪነታቸው ለምርምር ዘርፍ ዳይሬክተሮች ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አለባቸው

6.1 የግብርና ልማት ፖሊሲዎች መሠረት በማድረግ የፕሮግራሙን ስትራቴጂ ይነድፋል፣ ቅደም ተከተል ይወስናል፣ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ያወጣል፣ ሲፀድቅም በሚመለከታቸው ተመራማሪዎች በኩል ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

6.2 ከአገሪቱ የልማት አቅጣጫ እና ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ የምርምር ሥራዎችን ይቀርጻል፣ ይገመግማል፣ ያፀድቃል፣ በበጀት በመደገፍ በተመራማሪዎች በኩል ተግባራዊ ያደርጋል፤

6.3 ለተጠናቀቁ የምርምር ሥራዎች የግምገማ መድረክ በማዘጋጀት ያስገመግማል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ውጤቶቹም እንዲታተሙ ያደርጋል፤

6.4 ከፕሮግራሙ የሚወጡ ቴክኖሎጂዎችንና መረጃዎችን በዕቅዱ መሰረት መውጣታቸውን ያረጋግጣል፣ ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

6.5 ወቅታዊነት ባላቸውና ፕሮግራሙን በሚመለከቱ አጀንዳዎች ላይ አገራዊ አውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት ለልማቱ ፈጣን የመረጃ አቅርቦት እንዲኖር ይሰራል፤

6.6 ከፕሮግራሙ የሚገኙትን የምርምር ውጤቶች መሰረት በማድረግ ልማቱን የሚያግዙ የአመራረትና የአሰራር መመሪያዎችን ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፣ ለቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎችና ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፤

6.7 በፕሮግራሙ የምርምር ስርዓቱን ለማዘመን የሚያስችሉ አዳዲስ አሰራሮችን እና ቴክኖሎጂዎች ለመጠቀም እንዲቻል የአቅም ግንባታ ድጋፍ እና የክትትል ያደርጋል፤

6.8 በፕሮግራሙ የሚመነጩትን አዳዲስ የምርምር መረጃዎች (ዳታ) ወደ መረጃ ቋት ሥርዓቱ እንዲገቡ ያደርጋል፤ በጥቅል መረጃዎቹ ላይ አዳዲስ ትንተናዎችን በመስራት የግብርና ችግሮችንና መፍትሄዎችን ሞዴል በማድረግ ይሰራል፤

6.9 ለፕሮግራሙ ተጨማሪ ኃብት ያፈላልጋል፣ ያመነጫል፤

6.10 በፕሮግራሙ ስር ያሉ ተመራማሪዎች የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፤ ክፍተታቸውን እየለየ ድጋፍ ያደርጋል፤

6.11 ለፕሮግራሙ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል እንዲሟላ ለሚመለከተው የዘርፍ ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

6.12 ሌሎች ከሚመለከተው የዘርፍ ዳይሬክቶሬት የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 7

የምርምር አመራር ምደባ የሚካሄድባቸው ሁኔታዎች

7.1 በሥራ ላይ ያለው የምርምር አመራር የሥራ ዘመን ሲጠናቀቅ፤

7.2 የአመራሩ የሥራ ዘመን ባይጠናቀቅም በተለያዩ ምክንያቶች አመራር መለወጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ (በአፈጻጸም ድክመት፣ በሕመም፣ በትምህርት፣ በሞት፣ በሹመት፣ በግል ጥያቄ እና ተመሳሳይነት ባላቸው ሌሎች ምክንያቶች) ከኃላፊነቱ ሲነሳ፤

7.3 የምርምር አመራሮች ምደባ በሦስት መንገዶች ማለትም በቀጥታ ምደባ፣ ማስታወቂያ በማውጣት በግልጽ ውድድር እና እንደአስፈላጊነቱ በሠራተኞች ምርጫ ሊፈፀም ይችላል።

አንቀጽ 8

በቀጥታ ስለመመደብ

8.1 የኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራር በበቂ አሳማኝ ምክንያት፣የትምህርት ደረጃ፣ የመምራት ብቃትና ዝግጅት አለው ብሎ ያመነበትን ተመራማሪ ዝቅተኛውን መስፈርት ካሟላ በቀጥታ የዘርፍ ዳይሬክተር ወይም የማዕከል ዳይሬክተር አድርጎ መመደብ ይችላል።

8.2 የሚመለከተው የዘርፍ ዳይሬክተር በበቂ አሳማኝ ምክንያት የመምራት ብቃትና ዝግጅት አለው ብሎ ያመነበትን ተመራማሪ ዝቅተኛውን መስፈርት ካሟላ የሚመለከተውን ምክትል ዋና ዳይሬክተር በማማከር በቀጥታ የፕሮግራም አስተባባሪ አድርጎ መመደብ ይችላል።

አንቀጽ 9
በውድድር ስለመመደብ

9.1 የኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራር አንድን ዳይሬክቶሬት ወይም ማዕከል የሚመራ አመራር ለመመደብ ግልጽ የሆነ የውስጥ ማስታዋቂያ እንዲወጣ ያደርጋል፤

9.2 የሚመለከተው የዘርፍ ዳይሬክቶሬት አንድን ፕሮግራም የሚመራ አመራር ለመመደብ ግልጽ የሆነ የውስጥ ማስታወቂያ እንዲወጣ ያደርጋል፤

9.3 ለምርምር አመራርነት የሚወዳደሩ አመልካቾች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ላይ በተቀመጡት ዝርዝር መስፈርቶች መሰረት እንዲመዘኑ ይደረጋል፤

9.4 ማስታዋቂያ ለወጣበት የአመራርነት ቦታ የሚወዳደሩ አመልካቾች መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ ከየትኛውም ማዕከል ወይም ዳይሬክቶሬት መሆን ይችላሉ፤

9.5 በዳይሬክተርነት ከተወዳደሩ አመልካቾች መካከል 75% እና በላይ ያገኘ ተወዳዳሪ ከሌለ ውድድሩ ለሁለተኛ ጊዜ እንዲደገም ~~ይደረጋል~~ ወይም በሌሎች የአመራር ምደባ መንገዶች መሰረት እንዲመደብ ሊደረግ ይችላል፡፡

አንቀጽ 10
በሠራተኞች ምርጫ ስለመመደብ

10.1 አንድን ማዕከል የሚመራ ዳይሬክተር ለመመደብ አሳማኝ የሆነ በቂ ምክንያት ሲኖር የሚመለከታቸው ሰራተኞች ዝቅተኛውን መስፈርት ካሟሉ ዕጩዎች መካከል በቀጥታ ተሳትፎ በሚካሄድ ምርጫ እንዲመርጡ ሊደረግ ይችላል፡፡

10.2 በዚህ የሠራተኞች ምርጫ የተሻለ ድምጽ ካላቸው ዕጩዎች ውስጥ ተቀራራቢ ድምጽ ካገኙ ሦስት ተወዳዳሪዎች ውስጥ የተሻለ የመምራት ብቃት አለው ተብሎ የሚታመንበት ተወዳዳሪ በበላይ አመራሩ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

10.3 በዚህ አንቀጽ 10.2 የተቀመጠው ~~ቢኖርም እንኳን~~ እንደተጠበቀ ሆኖ የበላይ አመራሩ ከቀረቡ ዕጩዎች ውስጥ የመምራት አቅም ያለው ተወዳዳሪ የለም የሚል አሳማኝ ምክንያት ካለው የተሻለ ብቃት ያለውን ግለሰብ በቀጥታ ምደባ ሊመድብ ይችላል፡፡

አንቀጽ 11
በምርምር አመራርነት ለመወዳደር መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች

11.1 ለምርምር ዘርፍ ዳይሬክቶሬቶች ዳይሬክትነት

11.1.1 በተመራማሪነት መደብ ላይ ያለ፣ ቢያንስ የማስተርስ ዲግሪ ያለው እና ከፍተኛ ተመራማሪ እና በላይ የሆነ እንዲሁም አስር ዓመትና በላይ በምርምር ልምድ ያለው፤

11.1.2 ቢያንስ በሶስት የጆርናል ጽሁፎች ወይም መጽሐፍ ወይም የመጽሐፍ ምዕራፍ የመጀመሪያ ፀሐፊ የሆነ፤

11.1.3 የሁለት ጊዜ አማካይ የሥራ አፈጻጸሙ ከፍተኛና በላይ የሆነ፤

11.1.4 ዕድሜው 55 ዓመትና በታች የሆነ፤

11.1.5 ቢያንስ በዘርፍ ዳይሬክተርነት ወይም በሥራ ሂደት አስተባባሪነት ወይም በውጭ ፕሮጀክት አስተባባሪነት ወይም በፕሮግራም አስተባባሪነት እና ከዚያ በላይ በሆኑ ኃላፊነቶች ላይ ለሦስት ዓመታት በውጤታማነት ያገለገለ፤

11.1.6 የዳይሬክቶሬቱን የውስጥና የውጪ ሁኔታዎች ጠንቅቆ በማወቅ በሙያው አርቆ-ማሰብን በመላበስ የመምራትና የማስተባበር ክህሎት ያለው፤

11.1.7 በመልካም ሥነ-ምግባሩ የተመሰገነ እና የመግባባት ክህሎት ያለው፤

11.1.8 ከዕጬነቱ በፊት ባሉት አምስት ዓመታት በወንጀልና በዲሲፕሊን ያልተቀጣ፤

11.1.9 በተከታታይ ከሁለት የአገልግሎት ዘመን በላይ በዘርፍ ዳይሬክተርነት ያላገለገለ፤

11.1.10 ከፍተኛ የሥራ ተነሳሽነት ያለው፤

11.2 ለማዕከል ዳይሬክተርነት

11.2.1 በተመራማሪነት መደብ ላይ ያለ፣ ቢያንስ የማስተርስ ዲግሪ ያለው፣ ቢያንስ ተመራማሪ I እና በላይ የሆነ እንዲሁም ስምንት ዓመትና በላይ ልምድ ያለው፤

11.2.3 ቢያንስ በሦስት የጆርናል ጽሁፎች ወይም መጽሐፍ ወይም የመጽሐፍ ምዕራፍ የመጀመሪያ ፀሐፊ የሆነ፤

11.2.3 የሁለት ጊዜ አማካይ የሥራ አፈጻጸሙ ከፍተኛ እና በላይ የሆነ፤

11.1.4 ዕድሜው 55 ዓመትና በታች የሆነ፤

11.1.5 ቢያንስ በሥራ ሂደት አስተባባሪነት፣ በውጭ ፕሮጀክት አስተባባሪነት፣ በፕሮግራም አስተባባሪነት እና በላይ በሆኑ ኃላፊነቶች ላይ ለሦስት ዓመታት በውጤታማነት ያገለገለ፤

11.2.2 የማዕከሉን የውስጥና የውጪ ሁኔታዎች ጠንቅቆ በማወቅ በሙያው አርቆ-ማሰብን በመላበስ የመምራትና የማስተባበር ክህሎት ያለው፤

11.2.3 በመልካም ሥነ-ምግባሩ የተመሰገነ እና የመግባባት ክህሎት ያለው፤

11.2.4 ከዕጬነቱ በፊት ባሉት አምስት ዓመታት በወንጀል ያልተቀጣ፤

11.2.5 በተከታታይ ከሁለት የአገልግሎት ዘመን በላይ በማዕከል ዳይሬክተርነት ያላገለገለ፤

11.2.6 ከፍተኛ የሥራ ተነሳሽነት ያለው፤

11.3 ለፕሮግራም አስተባባሪነት

11.3.1 በተመራማሪነት መደብ ላይ ያለ፣ ቢያንስ የማስተርስ ዲግሪ ያለው፣ ቢያንስ ተመራማሪ I እና በላይ የሆነ እንዲሁም ስምንት ዓመትና በላይ ልምድ ያለው፤

11.3.2 ቢያንስ በሦስት የጆርናል ጽሁፎች ወይም መጽሐፍ ወይም የመጽሐፍ ምዕራፍ የመጀመሪያ ፀሐፊ የሆነ፤

11.3.3 የሁለት ጊዜ አማካይ የሥራ አፈጻጸሙ ከከፍተኛ በላይ የሆነ፤

11.3.4 ዕድሜው 55 ዓመትና በታች የሆነ፤

11.3.5 ቢያንስ በሥራ ሂደት አስተባባሪነት፣ በውጭ ፕሮጀክት አስተባባሪነት፣ በፕሮግራም አስተባባሪነት እና በላይ በሆኑ ኃላፊነቶች ላይ ለሦስት ዓመታት በውጤታማነት ያገለገለ፤

11.3.6 የፕሮግራሙን የውስጥና የውጪ ሁኔታዎች ጠንቅቆ በማወቅ በሙያው የመምራትና የማስተባበር ክህሎት ያለው፤

11.3.7 በመልካም ሥነ-ምግባሩ የተመሰገነ እና የመግባባት ክህሎት ያለው፤

11.3.8 ከዕጩነቱ በፊት ባሉት አምስት ዓመታት በወንጀል ያልተቀጣ፤

11.3.9 በተከታታይ ከሁለት የአገልግሎት ዘመን በላይ በፕሮግራም አስተባባሪነት ያላገለገለ፤

11.3.10 ከፍተኛ የሥራ ተነሳሽነት ያለው፤

አንቀጽ 12

የአስመራጭ ቡድን አሰያየም

12.1 የማዕከል ዳይሬክተሩን በሠራተኞች እንዲመረጥ ማድረግ ሲያስፈልግ የኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራር አስመራጭ ኮሚቴ እንዲሰየም ያደርጋል፡፡

12.2 የኮሚቴው አባላት ሦስት ሲሆኑ፤

1) የማዕከል ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ----------- የኮሚቴው ሰብሳቢ
2) የዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት -------------------------- አባል
3) የብቃትና ሰው ኃብት አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ -----------አባልና ፀሐፊ

12.3 የአስመራጭ ኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን ለሁለት ዓመታት ብቻ ይሆናል፡፡ ነገር ግን የኮሚቴው የሥራ አፈጻጸም በበላይ አመራሩ ተገምግሞ የተሻለ ከሆነ ለተጨማሪ አንድ ዙር ሊራዘም ይችላል፡፡

አንቀጽ 13

የአስመራጭ ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

13.1 በዚህ መመሪያ መሠረት ምርጫውን ለማከናወን በቂ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፤

13.2 ለምርጫው ሂደት ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ማለትም የምርጫ ካርድ፣ ስለ ምርጫ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ጽሁፎችን ማዘጋጀት፣ በማዕከል ለምርጫው ሂደት ዝግጅት

መደረጉን መከታተል፣ ለሁሉም የማዕከሉ ሠራተኞች በምርጫው ዕለት እንዲገኙ ግልጽ በሆኑ ቦታዎች ላይ ማስታዋቂያ ማስለጠፍ፣ ለምርጫ ምቹ የሆነ አዳራሽ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፤

13.3 የምርጫውን ዓላማ፣ ይዘት፣ አፈጻጸሙን፣ ስለ ድምጽ አሰጣጡ ሂደት በስብሰባው ላይ ለተገኘው ሠራተኛ ማብራሪያ መስጠት፣ አስተያየትና ጥያቄ ተቀብሎ ምላሽ መስጠት፤

13.4 የምርጫ ሂደቱን የሚታዘብ የፆታን ስብጥር ባማከለ መልኩ ሦስት አባላት ያሉበት የአስመራጭ ኮሚቴ በሠራተኞች እንዲመረጡ ማድረግ (ከተመራማሪ 1፣ ከቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ 1 እና ከአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ዘርፍ 1) ይሆናል፡፡

13.5 የተመረጡት የምርጫ ታዛቢዎች ከአምስት ያልበለጡ ዕጩ ዳይሬክቶሮች ጥቆማ እንዲካሄድ በማድረግ ለአስመራጭ ኮሚቴው ያሳውቃሉ፡፡

13.6 አስመራጭ ኮሚቴው በአስር ቀናት ጊዜ ውስጥ የተጠቆሙት ዕጩ የማዕከል ዳይሬክተሮች ለሠራተኛው ከ 20 ደቂቃ ያልበለጠ የማዕከሉን ስትራቴጂክ ዕቅድ እንዲያቀርቡ ካደረገ በኋላ ድምጽ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

13.7 አስመራጭ ኮሚቴው ከዋና መሥሪያ ቤት ታሽጎ የተላከው የድምጽ መስጫ ወረቀት በአግባቡ መድረሱን ለመራጮች በማሳየት እንዲከፈት ያደርጋል፡፡

13.8 የድምፅ መስጫ ወረቀቱ የመምረጥ መብት ላላቸው ሠራተኞች እንዲታደል ማድረግና ሠራተኞች ድምጻቸውን ከሰጡ በኋላ በተዘጋጀው የድምፅ መስጫ ሳጥን እንዲያስቀምጡ ይደረጋል፡፡

13.9 በምርጫው ወቅት የተሰጡ ድምፆችን ከምርጫ ታዛቢዎች ጋር በመሆን መቁጠርና በዕለቱ ለሠራጠኞች ማሳወቅ፡፡

13.10 የተጠቃለለውን ለእያንዳንዱ ዕጩ የተሰጠውን ድምጽ ከምርጫ ታዛቢዎች ጋር በመፈራረም ውጤቱን ከቃለ-ጉባዔ ጋር በማያያዝ ለበላይ አመራሩ ያቀርባል፡፡

አንቀጽ 14
ለምርጫው ዝግጅት እና አፈጻጸም የባለድርሻዎች ኃላፊነት

14.1 በስራ ላይ ያለው የማዕከል ዳይሬክተር ወይም ተወካይ ኃላፊነት የማዕከሉ ቋሚ ሠራተኞች በምርጫው እንዲሳተፉ ለማድረግ ከአምስት የሥራ ቀናት አስቀድሞ የምርጫ ጥሪ በማድረግ ሁሉም ሠራተኞች መረጃው እንዲደርሳቸው ማድረግ፤

14.2 የማዕከሉ ቋሚ ሠራተኞች የሚጠበቅባቸው ኃላፊነቶች

14.2.1 ከአስመራጭ ኮሚቴውና ከታዛቢ ቡድኑ በሚሰጠው መግለጫና ማብራሪያ መሠረት የድምፅ መስጫ ወረቀቱን በአግባቡ መጠቀም፤

14.2.2 የምርጫው ሂደት ፍትህዊ እንዲሆን የበኩሉን ጥረት ማድረግ፤

14.2.3 ከማንኛውም የምርጫውን ሂደት ከሚያውክ ተግባር መቆጠብ፤

14.3 የማዕከል የምርጫ ታዛቢ ቡድን ኃላፊነት

14.3.1 መራጭ ሠራተኞች በተሠጣቸው የድምጽ መስጫ ካርድ መሰረት ድምጻቸውን እንዲሰጡ መከታተል፤

14.3.2 የአካል ጉዳተኛ መራጭ ሠራተኞች በምርጫው ሂደት ላይ ቅድሚያ እንዲያገኙ ማድረግ፤

14.3.3 የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ እንዳበቃ የድምጽ መስጫ ወረቀቱን ከምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴው ጋር በመሆን መቁጠርና መፈራረም፤

14.3.4 የምርጫ ድምጹን ውጤት በዕለቱ ማሳወቅ፤

አንቀጽ 15
የዕጩዎች ጥቆማ ሥርዓት

15.1 አንድ መራጭ ከአንድ ዕጩ በላይ መጠቆም አይችልም፡፡

15.2 በተጠቆሙ ዕጩዎች ላይ የድጋፍና ተቃውሞ ድምጽ እንዲሰጥ ይደረጋል፤ አሳማኝ ተቃውሞ የቀረበበት ዕጩ ከዕጩነት ይሰረዛል፡፡

አንቀጽ 16
የጽምፅ አሰጣጥ ሥርዓት

16.1 እያንዳንዱ መራጭ አንድ ድምጽ ብቻ ይኖረዋል፡፡

16.2 እያንዳንዱ ድምጽ እኩል ዋጋ ይኖረዋል፡፡

16.3 እያንዳንዱ መራጭ ድምፅ የሚሰጠው ለድምፅ አሰጣጥ እንዲያመች በተዘጋጀው ካርድ ላይ ብቻ ነው፡፡

16.4 እያንዳንዱ መራጭ ድምጽ ለመስጠት በድምጽ መስጫ ካርዱ ላይ የአንድ ዕጩ ስም ብቻ መጻፍ ይኖርበታል፤ መራጩ በድምጽ መስጫው ላይ ከአንድ ዕጩ በላይ ስም ከጻፈ የሰጠው ድምፅ ውድቅ ይሆናል፡፡

16.5 መራጮች በድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ የራሳቸውን ስም መጻፍ ወይም መፈረም የለባቸውም፡፡

16.6 በምርጫ ላይ መሳተፍ የሚችሉት የሙከራ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ቋሚ ሠራተኞች ብቻ ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ 17

የድምጽ ውጤት ስለማጠቃለል እና ውሳኔስለመስጠት

17.1 አስመራጭ ኮሚቴው የምርጫ ውጤቱን ከማዕከሉ ታዛቢ ቡድን ጋር ተፈራርሞ ለማዕከሉ ሠራተኞች ከገለጸ በኋላ ሪፖርቱን ከቃለ-ጉባዔ ጋር በማያያዝ ለተቋሙ የበላይ አመራር በሦስት የሥራ ቀናት ያቀርባል፡፡

17.2 የበላይ አመራሩም የቀረቡትን ዕጩዎች ሁኔታ ከገመገመ በኋላ ከቀረቡት ውስጥ አንዱን ዕጩ በመምረጥ በማዕከል ዳይሬክተርነት ይመድባል፡፡

አንቀጽ 18

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

18.1 የምርምር አመራሩ ለኢንስቲትዩቱ ወይም ለማዕከሉ ጥቅም ብሎ በቅን ልቦና ለሚወስናቸው ውሳኔዎች ከበላይ አመራሩ ከለላ ይደረግለታል፡፡

18.2 የምርምር አመራሩ በሥራ አፈጻጸሙ ጉልህ ድክመት ካላሳየ ወይም በሕግ የሚያስጠይቅ ጥፋት ካልፈጸመ ወይም የኢንስቲትዩቱና የማዕከሉን ጥቅም በሚጎዳ ተግባር ውስጥ ተሳትፎ ካልተገኘ ወይም በራሱ ፍላጎት የመልቀቂያ ጥያቄ ካላቀረበ በስተቀር ለአንድ የአገልግሎት ዘመን ማገልገል ይችላል፡፡

18.3 የአገልግሎት ዘመኑን በጥሩ አፈጻጸም ያጠናቀቀ የዘርፍ ወይም የማዕከል ዳይሬክተር የመማር ፍላጎት ካለው ያለምንም ውድድር የትምህርት ዕድል እንዲያገኝ ይደረጋል፤ የመማር ፍላጎት ከሌለውና ባለበት ማዕከል ውስጥ ቢያንስ ለአስር ዓመታት ካገለገለ በስራ ዘርፉ ተመሳሳይ ቦታ ከተገኘ ወደሚፈልገው ማዕከል ያለውድድር እንዲዘወር ይደረጋል፡፡

18.4 አገልግሎቱን ሲያጠናቅቅ የክብር የምስክር ወረቀት በተቋሙ የበላይ አመራር ተፈርሞ ይሰጠዋል፡፡

አንቀጽ 19

ስለ መመሪያው ~~ገዥነት~~ ተፈጻሚነት

የግብርና ምርምር አመራርን ምደባ በሚመለከት ከዚህ መመሪያ ጋር የሚጋጭ ማንኛውም ተቋማዊ መመሪያ፣ አሰራር ወይም ውሳኔ ይህ መመሪያ ፀድቆ በስራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

አንቀጽ 20

የዲስፐሊን ቅጣትን በተመለከተ

የዚህን መመሪያ አፈጻጸም ሆን ብሎ የሚያውክ ወይም በማንኛውም ሁኔታ የሚጥስ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ በፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010፣ በወንጀል ህጎችና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ተጠያቂ ይደረጋል።

አንቀጽ 21

ስለመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ ከዛሬ ____________________2016 ዓ.ም ጀምሮ ፀድቆ በሥራ ላይ ውሏል።

ዋና ዳይሬክተር

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

አባሪ፡ አንድ

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

የምርምር አመራር ማወዳደሪያ መስፈርቶችና የነጥብ

ስሌት

ተ.ቁ	የማወዳደሪያ መስፈርቶች	የተሰጠው ነጥብ	መግለጫ
1	የትምህርት ዝግጅት	15	
1.1	የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ	15	
1.2	የማስተርስ ዲግሪ	10	
2	የሥራ ልምድ	10	
2.1	15 ዓመት እና በላይ	10	
2.2	10 ዓመት እና በላይ	7	
2.3	8 ዓመት እና በላይ	5	
3	የጆርናል ሕትመት ዋጋ	10	
3.1	5 የህትመት ዋጋ እና በላይ	10	
3.2	3 የህትመት ዋጋ እና በላይ	8	
3.3	ከ 3 የህትመት ዋጋ በታች	5	
4	የመምራት አቅም (በውድድር ወቅት በተቋሙ ማኔጅመንትና ሌሎች ተጋባዥ እንግዶች ፊት ቀርቦ በሚያቀርበው ዝርዝር የሥራ ዕቅድና በሚያቀርባቸው አዳዲስ አስተሳሰቦች መሰረት የሚለካ ነው፡፡)	25	ውጤቱ የሚሰላው 5 ገምጋሚዎች በየግል ከ 25% የሚሠጡት አማካይ ነው፡፡
5	የተግባቦት ክህሎት (ከውስጥና ከውጭ አካላት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በሚመለከት በሚያቀርበው ዕቅድ የሚለካ ነው፡፡)	15	ውጤቱ የሚሰላው 5 ገምጋሚዎች በየግል ከ 15% የሚሠጡት አማካይ ነው፡፡
6	ተጨማሪ ኃብት የመፍጠር ዕቅድ	10	ውጤቱ የሚሰላው 5 ገምጋሚዎች በየግል ከ 10%
			የሚሠጡት አማካይ ነው፡፡
	የበላይ አመራሩ አስተያየት	10	
8	የዶክመንት ጥራት /ሥነ-ምግባር/	5	
	ድምር	100	

- እያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪ ከላይ በቀረቡት መመዘኛዎች መሰረት ከተገመገመ በኃላ የተሻለ ውጤት ያገኘው የውድድሩ አሸናፊ ይሆናል፡፡

አባሪ፡ ሁለት

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

በማዕከል ዳይሬክተር ምርጫ ሂደት የድምፅ ውጤት ማሳወቂያ ቅጽ

ማዕከል: ______________________________

ተ.ቁ	የዕጩዎች ሙሉ ሥም	የድምፅ ብዛት			ጠቅላላ የድምጽ ብዛት	ደረጃ
		የተመራማ	የቴክ/ድጋፍ ሰጪ	የአስ/ ድጋፍ ሰጪ		
		የድምፅ ብዛት	የድምፅ ብዛት	የድምፅ ብዛት		
1						
2						
3						
4						
5						
6						
7						

የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ሥም:

1) ______________________ ፊርማ: _____________

2) ______________________ ፊርማ: _____________

3) ______________________ ፊርማ: _____________

የታዛቢ ቡድን አባላት ሥም:

1) ______________________ ፊርማ: _____________

2) ______________________ ፊርማ: _____________

3) ______________________ ፊርማ: _____________

አባሪ፡ ሦስት

<u>የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት</u>

<u>የማዕከል ዳይሬክተር መምረጫ ካርድ</u>

ለ ____ ማዕከል

ዳይሬክተርነት ከቀረቡ ዕጩዎች ውስጥ በእርስዎ እምነት ማዕከሉን በአግባቡ መምራት ይችላል የሚሉትን ዕጩ ሙሉ ስም ብቻ ከዚህ በታች ባለው ክፍት ቦታ ላይ ይሙሉ፡፡

ዶ/ር/ አቶ/ ወ/ሮ /ወ/ሪት ____

<u>የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት</u>

<u>የማዕከል ዳይሬክተር ምርጫ ካርድ</u>

ለ ____ ማዕከል

ዳይሬክተርነት ከቀረቡ ዕጩዎች ውስጥ በእርስዎ እምነት ማዕከሉን በአግባቡ መምራት ይችላል የሚሉትን ዕጩ ሙሉ ስም ብቻ ከዚህ በታች ባለው ክፍት ቦታ ላይ ይሙሉ፡፡

ዶ/ር/ አቶ/ ወ/ሮ /ወ/ሪት ____

<u>የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት</u>

<u>የማዕከል ዳይሬክተር ምርጫ ካርድ</u>

ለ ____ ማዕከል

ዳይሬክተርነት ከቀረቡ ዕጩዎች ውስጥ በእርስዎ እምነት ማዕከሉን በአግባቡ መምራት ይችላል የሚሉትን ዕጩ ሙሉ ስም ብቻ ከዚህ በታች ባለው ክፍት ቦታ ላይ ይሙሉ፡፡

ዶ/ር/ አቶ/ ወ/ሮ /ወ/ሪት ___________________________________